# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 181 ጥቅምት 23 2004 ገጽ 1


በአርባ ምንጭና በዋካ እንዳየነው የህዝባዊ እምቢተኝነት ፍንጮች እዚህም እዚያም እየታዩ ነው። ዛሬ እነዚህ የተናጠል እርምጃዎች ቢመስሉም በአፋጣኝ መቀናጀታቸው አይቀርም። በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ "የኔ ተሳትፎ ኢምንት ነው" ሳይል በተቻለው ሁሉ ትግሉን የሚያግዝበት ወቅት ላይ ደርሰናል ብሎ ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያምናል። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የቀድሞው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ፕሬዚዳንት የነበረው ያረጋል አይሸሹም ንብረት በወያኔ ፍርድ ቤት ታገደ። የግለሰቡ ሃብት ባለሥልጣናቱ የተዘፈቁበትን ሙስና መጠን አመልካች ነው ተባል

በያረጋል አይሸሹምና በህወሀት ባለስልጣናት መካከል በተነሳው የፖለቲካ ውዝግብ ምክንያት ቀደም ሲል ታማኝነቱንና ታዛዥነቱን ለማግኘት ሲባል በተከፈተለት የሙስና በር በራሱና በቤተሰብቹ ስም እስከዛሬ ያከማቸው ሃብትና ንብረት እንዳይንቀሳቀስ የወያኔ ፍርድ ቤት ማገዱን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርት ገለጸ።

ፍርድ ቤት ተብዬው የወያኔ የማጥቂያ መሳሪያ፤ በያረጋል አይሸሹም፤ በባለቤቱ በትግስት በቃልና፣ በልጆቹ ስም ተመዝግበው የሚገኙ ንብረቶችን ያገደው፤ በአሶሳ በ1200 ስኩየር መሬት ላይ የሰፈረ የግል መኖሪያ ቤትና ሌላ ተጨማሪ 1000 ካሬ ሜትር ቦታ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ አካባቢ የሚገኝ 500 ካሬ መሬት፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ የሚገኝ 4132 ካሬ ቦታ፣ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ 500 ስኩየር ሜትር ላይ የሰፈረ በአለአንድ ፎቅ ህንጻና አንድ ሌላ የኮንዶሚኒየም ቤት፣ ምግብ ቤት እንዲሁም በልጁ ስም የተመዘገበ 1490 ካሬ መሬት ቦታ እንደሆነ ታውቆአል።

ወያኔ ወደስልጣን በመጣበት ወቅት ለእግራቸው መቀየሪያ ጫማ ያልነበራቸው እንደ ያረጋል አይሸሹም አይነቶቹ ሆድ አደሮች፤ የአገሪቱን ሃብት በመዝረፍ አሉ ከሚባሉ ከበርቴዎች ተርታ መሰለፋቸው ተደጋግሞ ሲዘገብ የቆየ ቢሆንም፤ 8 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ዘርፎ በሲዊዝ ባንክ አስቀምጦአል ተብሎ ለአመታት እስር ቤት ተወርውሮ ከነበረው የቀድሞው የብአዴን መሪ ታምራት ላይኔና የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት አባተ ኪሾ ክሶች ወዲህ የሃብቱ ዝርዝር አደባባይ የወጣ የወያኔ ባለሥልጣን እንደሌለ ይታወቃል። ለዚህ ይመስላል የአሁኑ የያረጋል አይሸሹም ሃብት ዝርዝር ይፋ መውጣት ከህወሀት ባለስልጣናት ጋር የገባበትን የፖለቲካ ውዝግብ ተከትሎ የተወሰደ እርምጃ እንደሆነ በርካታ የህዝብ አስተያየቶች እየተሰነዘሩ ነው።

ያረጋል አይሸሹም ወያኔን ከመቀላቀሉ በፊት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የነበረ ሲሆን በወገንና በአገር ኪሣራ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ላለፉት 20 አመታት የመለስ ዜናዊ ቡድን ተጠናክሮ ስልጣን ላይ እንዲቆይ አቅማቸው የቻለውን ሁሉ አስተዋጾ ካበረከቱት ታማኝና ታዛዥ የወያኔ ሎሌዎች አንዱ እንደነበር ይታወቃል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ ለከፋፍለህ ግዛ አላማው የሙስሊሙን ማህበረሰብ ለሁለት መክፈሉና አክራሪ ያላቸውን ወገኖች በማሳደድ ላይ መሆኑ ያስነሳው ውዝግብ ውጥረት መፍጠሩ ተዘገበ

በከፋፍለህ ግዛ የቅኝ ገዥዎች ፖሊሲ የተለከፈው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በብሄር ብሄረሰቦች መካከል የፈጠረው ክፍፍል የታሰበውን ውጤት ስላላመጣለት ፊትን ወደ ሃይማኖት ተቋማት በመመለስ የሙስሊሙን ህብረተሰብ ለሁለት ጎራ የሚከፍል ተግባር እያራመደ መሆኑን በዚህም አብዛኛው የሙስሊም ሃይማኖት ተከታዮች ከፍተኛ የሆነ ቅሬታ እንዳደረባቸው የግንቦት 7 ዘጋቢ ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በአገራችን ሙስሊሞች ዘንድ ቀደም ሲል እውቅና ያልነበረው አህባሽ የሚባል የእምነት ትምህርት በወያኔ አገዛዝ የገንዘብና የሰው ሃይል ድጋፍ እየተደረገለት በሰፊው እየተሰራጨ እንደሆነና በሌላ በኩል ግን ሌላውን ወገን ዋህቢ በማለት በአክራሪነት ፈርጆአቸዋል። አዲሱን የአህባሽ ትምህርት የሚቃወሙ በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች የሚገኙ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ለእስር ከመዳረጋቸውም በተጨማሪ በአዲስ ዘመን ከተማ ነዋሪ የሆኑ የወረዳው የእስልምና ሀላፊ የነበሩት ሰው በታጣቂዎች መገደላቸው ታውቋል።

ወያኔ በሙስሊም እምነት መካከል እያደረገ ያለውን ክፍፍል የዘገበው የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን፤ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በፖሊሲ ደረጃ ቀርጾና በ10 ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ መድቦ የሙስሊሙ ማህበረሰብ አህባሽን እንዲከተል የማስገደዱን እርምጃ የተቃወሙ በርካታ የሀይማኖቱ ኡላማዎች ለስግደት ወደ ሳውዲ አረቢያ ከሄዱበት እንደማይመለሱ ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ያገኘውን መረጃ ገልጾ ይፋ አድርጎአል።

ከፋፋዩ ወያኔ ኢትዮጵያዊያንን በሃይማኖት መከፋፈልና ማጋጨት የጀመረው ወደስልጣን ወምበር ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን ቀደም (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የፋሽስቱ የወያኔ አገዛዝ ፖሊሲ ባስከተለው የኑሮ ደረጃ ግሽበት ተስፋ የቆረጡ ዘጎች አገራቸውን ጥለው በብዛት እየተሰደዱ መሆኑ ተገለጠ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ አንስቶ ሃገራቸውን ለቀው ለስደት የሚዳረጉት ኢትዮጵያዊያን ቁጥር እጅግ እያሻቀበ መምጣቱና በታሪክ ታይቶ ከማይታወቅ ደረጃ ላይ መድረሱ ታወቀ።

ሃገሪቱን ለቀው ወደውጪ ሃገራት በሚሰደዱ ኢትዮጵያዊያን ዙሪያ ለሚጠናቀረው መረጃ ቅርብ የሆኑ የውስጥ ምንጮቻችን እንዳረጋገጡት በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያን በመልቀቅ ወደ የመንና ሱዳን የሚሰደዱት ኢትዮጵያዊያን ብዛት በእጅጉ አስደንጋጭ እየሆነ መጥቱአል።

ዘጋቢያችን የውስጥ ምንጮቹን በመጥቀስ በላከልን ዘገባ ላይ እንዳመለከተው፣ በተለይም ከአማራ ክልል ሃገራቸውንና ቀያቸውን ለቀው የሚሰደዱ ኢትዮጵያዊያን የከተማ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ገበሬዎች ጭምር መሆናቸው ታውቁአል። መረጃዎቹ እንዳረጋገጡት በደቡብ ጎንደር በየሳምንቱ ከ250 እስከ 300፣ በሰሜን ወሎ ከ300 እስከ 450፣ በደቡብ ወሎ ከ200 እስከ 300፣ በጎጃም ከ400 እስከ 550 የሚደርሱ ገበሬዎችና የከተማ ነዋሪዎች ወደ የመን፣ ሱዳንና ሌሎች የጎረቤት አገሮች በገፍ እንደሚሰደዱ ለማወቅ ተቺሉአል።

በተለይም ከአማራው ክልል ሃገራቸውን ለቀው የሚሰደዱት ኢትዮጵያዊያን ቁጥር ያሻቀበበት ዋነኛ ምክንያት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ማለቂያ የሌለው በደል፣ በየጊዜው የሚጨምረው የኑሮ ውድነት እና የእርሻ መሬት ጥበት መሆናቸው ታውቁአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ካለው እኩይ ፍላጎት የተነሳ የተወሰኑትን በሽብርተኝነት፣ ሌሎችን፣ በሃይማኖት እንዲሁም አብዛኛውን ህዝብ በጠመንጃ ሃይል በማስፈራራት ላይ መሆኑ በስፋት ሲዘገብ የቆየ ከመሆኑም በላይ የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የእርሻ ምነሬት እጦት እንዲሁም አለ የሚባለው ለም መሬት ለውጭ ባለሀብቶች እየተሰጠ መሆኑ ችግሩን እንዳባባሰው በርካቶች ይስማማሉ።

## ጥቅምት 22 ቀን 1998 በአረመኔው የወያኔ አገዛዝ የተጨፈጨፉ ሰማዕታት ስድስተኛ አመት ተዘከረ

ድህረ ምርጫ 97 የሰጠነው የምርጫ ድምፃችን ይከበርልን በማለታቸው ልክ የዛሬ 6 አመት ጥቅምት 22 ቀን 1998 . በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች ጎዳናዎች ላይ በአረመኔው የወያኔ አገዛዝ አጋዚ ጥይት በግፍ የተጨፈጨፉ፤ አካሎቻቸውን ያጡ፤ የተደበደቡ እና የተጋዙት ሰማእታት ወገኖቻችን 6ኛ አመት በሚሊየኖች በሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ እየተዘከረ ነው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በወርሃ ጥቅምት 1998 በንጹሃን ወገኖቻችን ላይ የፈጸመውን ያንን ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ ለማስታወስ የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው አንድ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ አመራር አባል እንደገለጹት መለስ ዜናዊ የህዝብ ፈቃድ በመፈጸም ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር በአገራችን እንዲጀመር ባለመፈለጉ በወሰደው በዚያ ዘግናኝ አረመኔያዊ እርምጃ ምክንያት ተስፋ ተሰንጎበት የነበረው አገራችንን ወደተሻለ የአስተዳደር ምዕራፍ የመውሰድ ጥረት ተቀልብሶ ሁላችንም ከዜሮ ለመጀመር ወደሚከድበት የትግል መስመር ተፍተናል ብለዋል። በዚህም የተነሳ የአገራችንና የህዝባችን ደህንነት ብቻ ሳይሆን ሰላማዊውንና ዲሞክራሲያዊውን ጎዳና በመቀልበስ መለስ ዜናዊ ለራሱና ለቤተሰቦቹ ታላቅ አደጋን ከፊቱ ደቅኖአል በማለት በቅርቡ በቱኒዚያ፤ በግብጽ፤ በሊቢያና በተቀሩት የአረብ አገሮች እየተደርገ ያለውን ሁኔታ አመልክተዋል።

የዛሬ 6 አመት ከተፈጸመው ጭፍጨፋ ባልተናነሰ ወገኖቻችንን በፍርሃትና በሽብር እያርበደበደ እስከወዲያኛው ለመግዛት የሚያልመው መለስ ዜናዊ በአሁኑ ሰዓት አፍንጫው አጠገብ እየሆነ ያለውን አዳድስ ኩነቶች ተመልክቶ ወደሚያዋጣው ሰላማዊ መድረክ እራሱን ከመመለስ ይልቅ ዛሬም በዚያው ድንቁርናና እብሪት እየተመራ ነው ያሉት የአመራር አባል በደመወዝ ተቀጥሮ በሚያገለግል ከህዝብ አብራክ በወጣ ተመንጃ ተሸካሚ ተማምኖና ተኮፍሰው ንቀት ማሳየት ለሊቢያው ሙአመር ጋዳፊም እንዳልበጀው በአይናችን ተመልክተናል ብለዋል።

ከንቀታቸውና ከእብሪታቸው ብዛት የተነሳ ለውጥ ፈላጊ ሊቢያዊያንን "አይጦች፣ በረሮች፣ ሃሽሻሞች፣ ዱሪየዎች ወዘተ ሲሉ የነበሩት ሙአመር ጋዳፊን መጨረሻ የተመለከተ፤ መለስ ዜናዊ ከምርጫ 97 ጀምሮ እያሰማ ያለው ድንፋታና ዛቻ የቁልቁለት ጎዳና ላይ መሆኑን ያመላክታልና የጥቅምት 22 ሰማ ዕታት የህይወት ዋጋ በከንቱ እንዳይቀር ሁላችንም ተባብረን መታገል ይጠበቅብናል ብለዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ የዛሬ 6 አመት የተጨፈጨፉትን እነዚህን ሰማእታት ለማስታወስ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ጋዳፊ ተገደሉ፤ መለስ ይፎከራል፤ ህዝብ ተማሯል!!!

ጥቅምት ወር ሲመጣ … "በግንቦት 7 1997 የሰጠነው የምርጫ ድምፃችን ይቆጠርልን!" በማለታቸው በጥቅምት 1998 ዓ.ም. በአዲስ አበባና ሌሎችም ከተሞች ጎዳናዎች በአጋዚ ጥይት በግፍ የተገደሉ፤ ለአካል ጉዳት የተዳረጉ፤ የተደበደቡ እና የተጋዙ ወገኖቻችንን በሃዘንና በቁጭት እናስታውሳለን።

ዘንድሮ የጥቅምት 98 ሰማዕታትን በምንዘክርበት ወቅት ሶስት አዳዲስ ኩነቶች ተደራርበው መጥተዋል። እነዚህ ኩነቶች የተለያዩ ቢመስሉም በአንድነት ሲጤኑ እየሄድንበት ያለውን መንገድ የሚያሳዩ በመሆናቸው አዛምደን ልናቀርባቸው ወሰነን።

1. **የሊቢያው ጋዳፊ አብዝተው ፎክረው ነበር፤ ግን ተዋርደው ተገደሉ**
   የሊቢያው ኮሎኔል ሙዓመር ጋዳፊ አብዮተኖችን "አይጦች፣ በረሮች፣ ሃሽሻሞች፣ ዱሪየዎች በመሆናቸው ቤት ለቤት እየሄዳችሁ፣ እያሳደዳችሁ ግደሏቸው!" ሲሉ "ይወደኛል" ለሚሉት ህዝብ ትዕዛዝ ሰጥተው ነበር። ሆኖም ግን ይነሳልኛል ያሉት ህዝብ ተነስቶባቸው በያዝነው ጥቅምት ወር ታሪካቸው በአሳዛኝ አጨራረስ ተደመደመ። ጋዳፊ እጎርፍ መውረጃ ቱቦ ውስጥ ተያዙ፣ ቆሰሉ፣ ተጎተቱ፣ ተዋረዱ፣ ሞቱ። ልጆቻቸውም ከፊሉ ተገደሉ፤ ሌሎቹ ተሰደዱ። አልጋቸውን ይወርሳል ይባል የነበረው ሰይፍ አል-ኢስላም ሄይግ ለሚገኘው ዓለም ዓቀፍ ችሎት እጁን ለመስጠት እየተደራደረ ነው የሚል ወሬ እየነፈሰ ነው።
2. **መለስ ዜናዊ አብዝቶ እየፎከረ ነው**
   ሰሞኑን ዘረኛው መለስ ዜናዊ እንደ ጋዳፊ ሁሉ በትዕቢት፣ ድንፋታ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ የታጀበ ንግግር አድርጓል። እሱም ልክ እንደጋዳፊ ጋዜጠኞችንና የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችን "ጋጠ ወጦችና ወንጀለኞች" እያለ ሁሉም ሰብስቦ ማሰር እንደሚችል ዝቷል። "የሚንጣጡ ጋዜጠኞች" አርፈው እንዲቀመጡም አስጠንቅቋል። መለስ ዜናዊ ልክ እንደ ጋዳፊ ቃላት አይመርጥም። አረንጓዴውን መጽሃፍ ከማገላበጥ በስተቀር ጋዳፊን ለመሆን የቀረው ነገር የለም።
3. **የህዝብ ምሬት መገንፈል ጀምሯል**
   በደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በዳውሮ ዞን የሚገኘው የዋካ ከተማ ህዝብ በአስተዳደር በደል፣ በኑሮ ውድነትና በወረዳ አከላል መነሻነት ተቃውሞ ቀስቅሷል። የዞኑ ካድሬዎች "በእያንዳንዳችሁ በር ላይ ድንኳን ይተከላል፤ ሞት ይዘራባችኋል!" እያሉ ቢያስፈራሩም ህዝቡ ግን "የመብት ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ወደኋላ አንልም" ብሎዓል። ትምህርት ቤቶች ተዘግተዋል፤ ዋካ በፌደራል ፓሊስ ተወራለች። በአርባ ምንጭም ከወራት በፊት የተቀሰቀሰው ተቃውሞ እስካሁን አልበረደም። በየቦታው ዜጎች እየታሰሩና እየተደበደቡ ቢሆንም ትግሉ ቀጥሏል። በመላ ሃገሪቱ ቁጭትና ምሬት በዝቷል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በሃይማኖት ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ እየገባ ምዕመናንን ለማበጣበጥ የሚያደርገው ጥረት እጅግ መራር የሆነ ተቃውሞን እየፈጠረ ነው። በአሁኑ ሰዓት በተለይ በእስልምና እምነት ውስጥ የሚደረገው ጣልቃ ገብነትና ፍረጃ ሞስሊሙን ማኅበረሰብ በእጅጉ አስቆጥቷል።

ከላይ የሰፈሩት ሶስት ነገሮች - የጋዳፊ የውርደት ሞት፤ የመለስ ዜናዊ ፉከራ እና እየተጠናከረ የመጣው የህዝብ ተቃውሞ - ከጥቅምት 98 ሰማዕታት ዝክር ጋር በአንድነት ሲታዩ የሚሰጠን አንድ አጠቃላይ ምስል አለ።

በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ለሃያ ዓመታት ተረግጠናል፤ ተዋርደናል፤ ተገድለናል። በሰላማዊ መንገድ መሪዎቻችንን ለመምረጥ የነበረን ህልም ተከርችሞ መዘጋቱ ካረጋገጥን እነሆ ስድስት ዓመታት ተቆጥረዋል። ሰማዕቶቻችንን የተሰውለት ዓላማ እስካሁን እግብ አለመድረሱ ይቆጨናል። ሆኖም ግን ሁኔታዎች እየተቀየሩ ነው።

ከመለስ ዜናዊ በላይ ያቅራሩና የፎከሩ አምባገነኖችም ተገርስሰዋል። ከሃያ አመታት በላይ ተቀጥቅጠው የተገዙ የቱኒዚያ፣ የግብጽና የሊቢያ ህዝቦች ዛሬ ነፃነታቸውን አረጋግጠዋል።

እኛም ዘንድ ፍንጮች እየታዩ ነው። "እኔ ምን አቅም አለኝ" የሚባልበት ወቅት አልፏል። የመለስ ዜናዊ የማስፈራሪያ "የፀረ-ሽብር" ህግ መሳለቂያ ሆኗል። "ለነፃነትና ለፍትህ መቆም 'ሽብርተኛ' የሚያስብል ከሆነ "እኔም ሽብርተኛ ነኝ" የሚሉ ድምፆች ከየአቅጣጫው እየተሰሙ ነው። በመለስ "የፀረ-ሽብር" ህግ የተከሰሱ ዜጎች ህዝብ "የነፃነት አርበኞች" እያለ ይጠራቸዋል።

> *ሁላችንም አንዱዓለም አራጌዎች፣ ሁላችንም እስክንድር ነጋዎች፤ ሁላችንም ደበበ እሸቱዎች፤ ሁላችንም ውብሸት ታዬዎች፣ ሁላችንም ርዕዮት ዓለሙዎች፣ ሁላችንም ስለሺ ሀጎሶች፣ ሁላችንም በቀለ ድሪባዎች፤ ሁላችንም አልባና ሌሊሳዎች ነን። አሁን ሁላችንም እስረኞች ነን። በቅርቡ ግን እስር ቤቶቻችንን ሰብረን ነፃ እንወጣለን!!!*

የሚል ድምጽ ከየአቅጣጫው እየተሰማ ነው።

በአርባ ምንጭና በዋካ እንዳየነው የህዝባዊ እምቢተኝነት ፍንጮች እዚህም እዚያም እየታዩ ነው። ዛሬ እነዚህ የተናጠል እርምጃዎች ቢመስሉም በአፋጣኝ መቀናጀታቸው አይቀርም። በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ "የኔ ተሳትፎ ኢምንት ነው" ሳይል በተቻለው ሁሉ ትግሉን የሚያግዝበት ወቅት ላይ ደርሰናል ብሎ ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያምናል።

ትናንሽ ነውጦች ሲጠራቀሙ ታላቁን ማዕበል አስነስተው ለመለስ ዜናዊ ትዕቢት የመጨረሻውን እልባት ይሰጣሉ ብሎ ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል። ማዕበሉ እየመጣ ነው!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

.................................................................................................................

## በቤልጂዩም የሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ ለአፍቃሪ ወያኔ ስደተኞችና ሆድ አደሮች ግብር ማብላቱ ተዘገበ

በአገር ውስጥ ያጣውን ድጋፍ በኢኮኖሚ ችግር ከተሰደዱትና ከወያኔ በመጠጋት ሊገኝ በሚችለው የጥቅም ትርፍራፊ ሊደለሉ የሚችሉ ግለሰቦችን በማሰባብሰብ ሊያገኝ ደፋ ቀና እያለ ያለው የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ ባለፈው ቅዳሜ ጥቅምት 18 በብራስልስ ከተማ ድል ያለ ድግስ አዘጋጅቶ ግብር ማብላቱን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከሥፍራው ከላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል።

በካሱ ኢላላ የሚመራው የቤልጂዬም የወያኔ ኤምባሲ ቀደም ሲል ለተጋባዦቹ ባሰራጨው የግብዣ ጥሪ ወረቀት ፤ የኢትዮጵያን አድስ አመት ለማክበርና የሂዳሴ ግድብ ቦንድ ሺያጭ በኤምባሲው መጀመሩን ለማብሰር የርሰፕሽን ግብዣ በኤምባሲው ስለተዘጋጀ እስከነቤተሰብዎ ተጋብዘዋል የሚል መልዕክት መተላለፉ ታውቆአል።

አገር ውስጥ በመኖር የአገሪቱን የድህነት ዕጣ እየተጋፈጡ ያሉ የመንግሥት ሠራተኞች፤ መምህራን፤ የፋብሪካ ሠራተኖችኛና በተለያዩ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ተቀጥረው የሚያገለግሉ ዜጎች በየጊዜው እየናረ በሄደው የኑሮ ውድነት እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን መመገብ እንደማይችሉ እየታወቀ፤ ያለውዴታቸው በግዴታ ቦንድ እንዲገዙ ተጽ ዕኖ የሚያደርግባቸው መንግሥት፤ ከባህር ማዶ በንጽፅር የተቀማጠለ ኑሮ የሚኖሩትን ስደተኞች ለማባበል ከዚያ ደሃ ህዝብ በሚሰበሰብ ገንዘብ ድል ያለ ድግስ ደግሶ ማብላት አገዛዙ የደረሰበትን የፖለቲካ ኪሳራ አመልካች ነው ተብሎአል።

በዘር ሃረግና በጥቅም ትስሥር ምክንያት የህወሃት ቁንጮ የሆነው መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ በአገራችንና በህዝባችን ላይ እየፈጸሙ ያሉት ክህደትና ሰቆቃ ለማየት የተሳናቸው እነዚህ ሆድ አደሮች፤ እንኳን ከሰው ልጅ ከቤት እንስሳ የሚተርፍ ትኩስ ምግብ በቆሻሻ መጣያ ገንዳ ውስጥ በሚጣልበት አገር ውስጥ ቁጭ ብለው፤ ለሆዳቸው ሲሉ የገዛ ወገኖቻቸውን የስቃይ ጣር የሚያራዝም የፖለቲካና የገንዘብ ድጋፍ ለማበርከት ኤምባሲው ባዘጋጀው ድግስ ላይ መገኘታቸው በአገሪቱ የሚኖሩትን የህዝብ ወገኖች ሁሉ አሳዝኖአል።

ወያኔ ባዘጋጀው በዚህ ግብር የማብላት ሥነ-ሥርዓት ላይ ከተገኙት አብዛኛዎቹ ወያኔ በሚያራምደው የዘር መድልዎ ተጠቃሚ በመሆን ለትምህረት ወደ ቤልጂዬምና ሆላንድ የተላኩ የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ በወያኔ የዘር ፖለቲካ ወገኖቻቸው ግንባር ቀደም የጥላቻ ሰለባ የሆኑና በወያኔ የአባይ ግድብ ግንባታ ፕሮፖጋንዳ የእርቅ ፊቱን የመለሰላቸው የመሰላቸው አንዳንድ ድኩማን መሆናቸው ታውቆአል።

በድግስ ሥነሥርዓቱ ላይ ተገኝቶ ዜናውን ያጠናከረው ዘጋቢያችን እንደገለጸው ጥሪ ከተደረገላቸው የኦሮሞና፤ የአፋር ኮሚኒቲ አንድም በድግሱ ላይ እንዳልተገኘ የታወቀ ሲሆን እስከ 500 ሰዎች ሊመጡ ይችላሉ ተብሎ በቻርተር አውሮጵላን ከአገር ቤት ተጭኖ የመጣው ብዛት ያለው ባህላዊ ምግብና ቅዱስ ግዩርጊስ ቢራ በመትረፉ፤ በግብዣው ላይ ከተገኙት አብዛኛዎቹ የተረፈውን ምግብ በፊስታል ተከፋፈለው ወደየቤታቸው መሄዳቸው ተዘግቦአል።

በግብዛው ላይ አጭር ንግግር ያደረገው ካሱ ኢላላ ወያኔ የዋሆችን ለማደኛ ስለፈጠረው የሂዳሰ ፕሮጄክት አጭር ድስኩር ካሰማ ቦኋላ "ዕለቱ በመብላትና በመጠጣት በጋራ የምንደሰትበት ቀን ስለሆነ ንግግር አላበዛባችሁም" በማለት በወያኔ ቤተመንግሥት ተዘጋጅቶ ለግብር የተላከው እንጀራና ወጥ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ጋር በአሽቃባጭ አሳላፊዎች ተስተናግዶአል።

በልጅዬም ከ300 አይነት ቢራዎች በላይ በማምረት የምትታወቅ አገር ሲትሆን በአለም በታላቅነቱ ከመጀመሪያዎቹ ተርታ የሆነው ስቴላ የተባለ ቢራ ፋብሪካ የሚገኘው ድግሱ ከተካሄደበት 30 ኪሎሜትር ረቀት ላይ ነው። ሆኖም ደካማ ዜጎችን በሆድ መደለልና ምርኮኛ ማድረግ የተዋጣላቸው የወያኔ መሪዎች የአንድ ቢራ ዋጋ ከሊትር ውሃ በታች በሆነበት አገር ለምን በአውሮጵላን ቢራ ጭኖ መላክ እንዳስፈለጋቸው ለጊዜው የታወቀ ነገር የለም።

# ህዝብን ማሸበር የመጨረሻዉን ቀን ያሳጥረዋል እንጂ አያስረዝመዉም

የኢትዮጵያ ህዝብ ያለፉት ሀያ አመታት ታሪክ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከወያኔና ወያኔ ተሸክሞ ካመጣቸዉ ኮተቶች ጋር የተያያዘ ነዉ። ይህ ደግሞ ወደንና ፈቅደን ያቀፍነዉ የታሪክ ምዕራፍ ሳይሆን እንደ ቀንበር በግድ የተጫነብን ዕዳ ነዉ። ለዚህም ይመስላል ወያኔ የተባለዉ ቃል በተነሳ ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ "ተዉ ስማኝ አገሬ ሲከፋኝ ነዉ መኖሬ" እያለ አንጀቱ ዉስጥ የሚነደዉ እሳት የሚቀዘቅዝ እየመሰለዉ በአፉ የሚተነፍሰዉ። ወያኔ ደርግን አሸንፎ የመጣ ኃይለ ቢሆንም መለስ ዜናዊንና ስብሐት ነጋን የመሳሰሉ መሰሪ መሪዎቹ፤ በኢትዮጵያና በህዝቧ ላይ ያላቸዉን ጥላቻ ያሳዩት ገና በጥዋቱ ስለነበረ ህዝቡ "ደሞ ምን ይመጣብኝ ይሆን" እያለ ጭንቀቱን ከመግለጽ ዉጭ ወያኔን ዬኔ ነዉ ብሎ አያዉቅም። ዛሬ ወያኔ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ሃያ ድፍን አመታት ተቀጥረዋል፤ ሆኖም ወያኔ እራሱ መንገዶችን፤ አደባባዮችንና አንዳንድ ተቋሞችን ወያኔያዊ ስም ያወጣላቸዉ አንደሆነ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሆነ ወያኔን በፍጥነት አስወግዶ ክፉ ትዝታዉን የሚያስረሳዉን ነገር እንጂ ወያኔን የሚያስታዉሰዉ ነገር በፍጹም አይፈልግም።

በዚህ በመገባደድ ላይ ባለዉ የፈረንጆቹ አመት በተለይ ከሰሜን አፍሪቃዉ የአረብ አብዮት በኋላ የወያኔ ፀባይ እንደ እርጉዝ ሴት በየቀኑ ሲቀያየር ይታያል። ባለፉት ሃያ አመታት ህዝብ የሚበላዉ አጥቶ ሲቸገር ኤኮኖሚዉ በድርብ አሃዝ አደገ እያሉና ሰላማዊ ህዝብ መኃል ገብተዉ ቦምብ እያፈነዱ በተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ እያላከኩ የከረሙት የወያኔ ጉደኞች በዚህ በያዝነዉ አመትማ ጭራሽ ብሶባቸዉ አላፊ አግዳሚዉን "ሽብርተኛ" እያሉ መክሰስ ጀምረዋል። ይህ የዘንድሮዉ "አላርፍ ያለች ጣት" አይነቱ የወያኔ አጉል .መንቀልቀልና የቀቢፀ ተስፋ እርምጃ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመጨረሻዉ ወሳኝ ትግል ከማዘጋጀቱ ባሻገር ህዝቡ "ሽብር"፤ "ሽብርተኛ"ና "አሸባሪ" የሚባሉ ቃላቶችን ከወትሮዉ በተለየ መልኩ እንዲጠቀምባቸዉ እያደረገዉ ነዉ።

መለስ ዜናዊ አዲስ አበባን ከረገጠበት ግዜ ጀምሮ አገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ የአገዛዙ ቅሌቶች ስትታመስ የቆየች ቢሆንም ይህ ከሰሞኑ የምናየዉ ቅሌት ግን ለጽድቅም ለኩነኔም የማይመች ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነዉ። መለስ ዜናዊ በአለም አቀፍ ደረጃ በሽብርተኝነት ላይ የሚካሄደዉ ጦርነት ያንን እስቀያሚ ገጽታዉን የሚሸፍንበትን የፖለቲካ ሽፋን እንደሰጠዉ በሚገባ ያዉቃል። ለዚህም ይመስላል የሽብርተኛዉ ብዛት ባደገ ቁጥር በአንድ በኩል የስልጣን ዘመኑ የሚራዘምለት እየመሰለዉና በሌላ በኩል ደግሞ የአሜሪካ መንግስት የሚሰጠዉ ድጎማ የሚጨምር እየመሰለዉ የኢትዮጲያን ህዝብ በደፈናዉ ሽብርተኛ ብሎ ለመጥራት የቀረዉ አንድ ሐሙስ ብቻ ይመስላል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋዜጠኛዉን፤ ደራሲዉን፤ አርቲስቱን፤ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዉን፤ አስተማሪዉንና ተማሪዉን ሽብርተኛ እያለ ማሰር ከጀመረ ሰንበት ብሏል። የሚገርመዉ ይህ አላፊ አግዳሚዉን ሽብርተኛ እያሉ ማሰር መለስ ዜናዊ አስካመነበት ድረስ ማንንም ሰዉ ያጠቃልላል። ለምሳሌ እስከዛሬ በአለም ላይ በሽብርተኝነት ቀርቶ በተራ ወንጀል እንኳን ስማቸዉ እምብዛም የማይጠራዉን የሲዊዲን ዜጎችም መለስ ዜናዊ ስላመነበት ብቻ ሽብርተኞች ተብለዉ ያልተበደሩትን ዕዳ እየከፈሉ ነዉ።

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በዚህም በዚያም ብለዉ አጣብቂኝ የበዛበት መስቀለኛ መንገድ ላይ ደርሰዋል። ከዚህ አጣበቂኝ ዉስጥ ለመዉጣት አማራጩ ከህዝብ ነፃነትና ከነሱ የበላይነት አንዱን መምረጥ አለባቸዉ። ይህ ምርጫ ደግሞ እንዳዉ የዘፈቀደ ምርጫ ሳይሆን ለአገር፤ ለወገንና ለራስ ታማኝ መሆንን የሚጠይቅ ምርጫ ነዉ። መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ በተፈጥሯቸዉ እንኳን ለአገርና ለወገን ለራሳቸዉና ለስሜታቸዉም የማይታመኑ ከሃዲዎች ናቸዉ። እንኳን የወደፊቱን የነገዉንም አያምኑምና ዉሳኔያቸዉ የአንድ ቀን፤ ምርጫቸዉ የአንድ ቀን፤ መሃላቸዉም የአንድ ቀን ነዉ። ስለዚህም ነዉ ህዝብን እያስለቀሱና ልጆቹን ከጉያዉ ጎትተዉ እስር ቤት እያጎሩ በዚያ እፍረት የሚባል ነገር በማያዉቀዉ አንደበታቸዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ሽብርተኞችን በማጋለጥ ላደረገልን ትብብር እናመሰግናለን የሚሉት። ነገሩ "ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነዉ" እንዲሉ ሆኖ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብማ ማን አሸባሪ ማን ተቀርቋሪ፤ ማን ለአገር አሳቢ ማን አገር ተሳዳቢ መሆኑን ካወቀ ሰንብቷል። ህዝብ የሚቆረቆሩለትን ልጆቹንና የሚዶልቱበትን ጠላቶቹን በዉል ለይቶ ያዉቃል። ይህንን ደግሞ ወያኔ ከሰሞኑ አላፊ አግዳሚዉን እያፈሰና ሽብርተኛ እያለ መዕከላዊ የሚሉት የምድር ላይ ሲዖል ዉስጥ ሲከታቸዉ - ህዝቡ በያለበት እስክንድር ሽብርተኛ ከሆነ እኛም ሽብርተኞች ነን፤ አንዱአለም አሸባሪ ከሆነ እኛም አሸባሪዎች ነን፤ደበበ እሼቱ የአሸባሪዎች ተባባሪ ከሆነ እኛም የአሸባሪዎች ተበባሪ ነን እየለ ተቃዉሞዉን በማሳየት ገልጿል። የሚገርመዉ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ "ሽብርተኝነት" "ጀግንነት" እያለ የወያኔን የፀረ ሽብር ህግና ወያኔ ሽብርተኞች እያለ የሚወስዳቸዉን እርምጃዎች መሳቂያና መሳለቂያ አድርጎታል። ወያኔም ቢሆን የፀረ ሽበር ህጉን ያወጣዉ የሚቃወሙትን ኃይሎች እያነቀ እስር ቤት ለመወርወር የሚያስችል ህጋዊ ሽፋን ለማግኘት ሲል ነዉ እንጂ እያሰረ የሚያሰቃያቸዉ ኢትዮጵያዉያን ሽብርተኞች አለመሆናቸዉንማ በሚገባ ያዉቃል። እጅግ በጣም ከሚገርሙን ነገሮች አንዱ ዛሬ በአለም አቀፍ ደረጃ አሸባሪ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ከፈፀሙት የሽብር ተግባር ጋር አያይዞ የሚመዘግበዉ ድርጅት ድህረ ገጽ ላይ ስማቸዉ ከሽብርተኝነት ጋር በቀጥታ ተያይዞ የሚገኘዉ መለስ ዜናዊ የሚመራዉ የህዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ ነዉ እንጂ ዉብሸት፤ አንዱአለም፤ እስክንድር፤ በቀለ፤ አላና፤ ወይመ ደበበ እሸቱ አይደሉም።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ብቻ ሳይሆን ነፃ የመገናኛ አዉታሮች በሌሉበት በዬትኛዉም አገር ቢሆን የፖለቲካ መሪዎች ያልሰሩትን ሠራን ያልጀመሩትን ጨረስን፤ ያልጋገሩትን አበሰልን ማለት ልማዳቸዉ ነዉ። መለስ ዜናዊ ደግሞ ተሳስቶም ቢሆን እዉነት ከተናገረ ነዉ "ምን ነካዉ" የሚባለዉ እንጂ ዉሸትማ ሲፈጠር ጀምሮ መታወቂያ ካርዱ ነዉ። በዬትኛዉም አገር ዉስጥ መንግስት፤ ሲቪል ማህበራትና ሌሎችም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግዴታቸዉን በሚገባ መወጣታቸዉን እየተከታተሉ ለህዝብ የማስታወቅ ሐላፊነት ያለባቸዉ የመገናኛ አዉታሮች ናቸዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ደግሞ ቴሌቪዥን፤ ሬዲዮና አዲስ ዘመንን የመሳሰሉ የዜና ማሰራጫ አዉታሮች የመንግስት ንብረት በመሆናቸዉ ያንኑ መንግስት የዋሸዉን ዉሸት መልሰዉ መላልሰዉ ከማስተጋባት የዘለለ ተግብር ማከናወን አይችሉም። የግል ጋዜጠኞች ደግሞ በተነፈሱ ቁጥር ዉሎና አዳራቸዉ ማዕከላዊና ቃሊቲ ሆኗል። ለኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ የመረጃ ምንጮች የነበሩት የአሜሪካና የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያዎች በወያኔ አፈና የተነሳ አስም እንደያዘዉ ሰዉ መነፋነፍ ከጀመሩ ቆይተዋል። በዉጭ አገር የሚገኙ የኢትዮጵያዉያን ድህረ ገፆች፤ ሬዲዮኖችና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ደግሞ እድሜ ለቻይና አገር ውስጥ እንዳይነበቡ ወይም እንዳይሰሙ ተደርገዋል። በነገራችን ላይ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያ ህዝብ ከአማራጭ ምንጮች መረጃ እንዳያገኝ ለማድረግ ብቻ በዉጭ ምንዛሪ የሚያወጣዉ ወጪ አገሪቱ ዉስጥ የደረሰዉን አስከፊ የረሀብ አደጋ ለመከላከልና ረሀብተኛዉን ለመቀለብ ከሚያወጣዉ ወጪ በአራት እጥፍ ይበልጣል። እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚያሳየን የመለስ ዜናዊ የአፈና ኃይል በግሉ ፕሬስ ላይ ያተኮረዉ እንደነ አስክንድር ነጋ፤ ዉብሸት ታዬና ርኢዮት አለሙን የመሳሰሉ የሾለ ብዕር ያላቸዉ ጋዜጠኞች መለስ ዜናዊን አላስዋሽ እያሉ ስላስቸገሩት ብቻ መሆኑን ነዉ።

መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት አደገ እያሉ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ሲያዉጁ አዉራምባ ታይምስንና ፍትህን የመሳሰሉ የግል ጋዜጦች - የታለ ዳቦዉ ህዝቡኮ እየተራበ ነዉ ይሉታል፤ የወያኔ የፕሮፓጋንዳ አዉታሮች የኢትዮጵያ ህዝብ የኢህአዴግን መመረጥ በመደገፍ ሠላማዊ ሠልፍ ወጣ ብለዉ ነጭ ዉሸት ሲዋሹ በግሉ ዘርፍ የተሰማሩ ጋዜጠኞች ደግሞ ከየመስሪያ ቤቱ ተገዶ ሠልፍ የወጣዉን ሰዉ በዋቤነት በማቅረብ ዉሸቱን በእዉነት ይቀይሩበታል። እንደዚህ አይነቱ በሞራል ትክክልኛነት ላይ የተመሰረተና ግልፅ የሆነ ጋዜጠኝነት ደግሞ ከደደቢት በረሃ ጀምሮ ነገረ ስራዉ ሁሉ ጨለማ ዉስጥ ብቻ ለሆነዉ ወያኔ በፍፁም የሚዋጥ አልሆነም። ደግሞስ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ከጫካዉ ወጡ እንጂ ጫካዉ ዛሬም ድረስ ከነመለስ ዜናዊ ዉስጥ አልወጣም፤ የወያኔ ሹሞች የሚኖሩት የጫካ ኑሮ፤የሚሰሩት የጫካ ስራ፤የሚመሩትም በጫካ ዉስጥ ህግ ነዉ፤ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ከፍተኛ ግጭት ዉስጥ የሚገቡትም በነሱ ግራ የተጋባ የጫካ ዉስጥ ህግ ከጫካዉ ዉጭ የሚኖረዉን ሠላማዊ ህዝብ እንዳኝህ ሲሉ ነዉ። እንግዲህ እነ መለስ ዜናዊ በነሱ የጫካ ህግ አልዳኝ ያለዉንና ባጠቃላይ ከነሱ ጋር አልስማማም ያለዉን ሁሉ እጅና እግሩን አስረዉ ማዕከላዊ እየወሰዱ ህይወቱን እስኪስት ድረስ አካሉንና የውስጥ ስሜቱን የሚያቆስሉት። እነመለስ ዜናዊ አለመግባባትን የሚያስወግዱት በአንድ መንገድ ብቻ ነዉ። በጠመንጃ!

ዛሬ እነመለስ ዜናዊ መስከረም ሲጠባ "ሽብር"፤ ህዳር ሲታጠን "ሽብር" ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተናገሩ ቁጥር "ሽብር"፤እያሉ እነሱ ተሸብረዉ ህዝብን የሚያሸብሩት እዉነትም ኢትዮጵያ ዉስጥ ሽብርተኞች ተፈጥረዉ አይደለም። ነገሩ "ጭር ሲል አልወድም" እንዳለቸዉ ወይዘሮ ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔ ቀንበር ከብዶት ለጥቂት ግዜም ቢሆን ዝም ካለ - ይህ ለወያኔ ሽብር ነዉ፤ ህዝብ ኑሮ ተወደደብኝ ብሎ አቤቱታ ካቀረበ ሽብር ነዉ፤ መብቴንና ነፃነቴን ብሎ ከታገለም ሽብር ነዉ። እንደ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ አባባል የኢትዮጵያ ህዝብ ሽብርተኛ የማይሆነዉ አፉን ዘግቶና አንገቱን ደፍቶ አሜን ብሎ ሲገዛላቸዉ ብቻ ነዉ። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለመብቱና ለነፃነቱ ለሚታገሉ ልጆቹ ሁሉ የሚዋጥ ሀቅ አይደለም። ስለሆነም ወያኔ ህዝብን አሸባሪ እንዳለ ህዝብም ወያኔን አሸባሪ እንዳለ የኢትዮጵያ ህዝብ መብት፤ ነፃነትና እኩልነት ሙሉ ለሙሉ እስከተከበረ ድረስ ትግሉ ይቀጥላል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔ በ2002 ዓም ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ብሎ ያረቀቀዉ ህግ ለህዝብ መብት፤ነፃነትና እኩልነት የሚታገሉ የሰላምና የዲሞክራሲ ኃይሎችን አስሮ ለመደብደብ ወይም ለመግደል እንዲያመቸዉና በተለይም በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ፊት ህጋዊ ሽፋን እንዲሆንለት የሚጠቀምበት ዘዴ መሆኑን በሚገባ ተረድቷል። ለዚህም ይመስላል ዛሬ ህዝቡ "ሽብርተኝነት" "ጀግንነት" ነዉ እያለ ወያኔ በሽብርተኝነት ስም ያሰራቸዉን እነ አስክንድር ነጋን፤ አንዱአለም አራጌን፤ ርኢዮት አለሙን፤ አላና ሌሊሳን፤ በቀለ ገርባን፤ ዉብሸት ታዬንና ሌሎችም ስማቸዉ የማይታወቅ የነፃነት ታጋዮችን "ጀግና" ብሎ መጥራት የጀመረዉ። እንግዲህ ካሁን በኃላ ሌላ ሁሉ ቢቀር ወያኔ የዘራዉ የከፋትና የዘረኝነት ዘር ከኢትዮጲያ ምድር ላይ አስኪነቀል ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ የልጆቹን ስም የሚሰይመው "ጀግናዬ" ለማለት "ሽብሬ" "ጀግናዉ" ለማለት ደግሞ "ሽብሩ" ብሎ ነዉ። በጣሊያን (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ አገዛዝ በንፁህ ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለውን የማሰር ተግባር በሁለተኛ ዙር ለማካሄድ እቅድ እንዳለው ተጋለጠ

አረመኔው የመለስ ወያኔ አገዛዝ የእስር ጥቃቱን ሲያካሄድ ዝግጅቱን ያጠናቀቀው በዋነኛነት በኦሮሞ፣ አጋዴንና አማራ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ተወላጆች ላይ መሆኑ ታውቅዋል። ይህ እቅድ ወያኔ ከሀምሌ ወር 2011 ጀምሮ እየተገበራቸው ካሉት ግዙፍ እኩይ ድርጊቶች ኢምንቱ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን ይህም ሀገር ውስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ ሀይላትን ከሀገር ጠራርጎ የማውጣት አላማን የተንተራሰ ዘዴ ነው።

መለስ ዜናዊ በቅርቡ በፓርላማ ስብሰባው ላይ በሰጠው መግለጫ መንግስት በርካታ ዜጎች ላይ እስር ለመፈፀም መረጃ እየሰበሰበ እንደሆነ በግልፅ ተናግሮዋል፣« ከአሸባሪ ቡድኖች ጋር እየሰሩ ያሉና ግንኙነት ያላቸው ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን፣ ከማሰራችን በፊት ጥቂት ተጨማሪ ማስረጃዎችን ብቻ ነው የምንፈልገው፣ በመቻኮል ሁሉንም ነገር ማበላሸት አንፈልግም» ነበር ያለው።

ይህ ቀጣዩ የጅምላ እስር እቅድ ያነጣጠረው ስጋት ሊሆኑ ይችላሉ እንዲሁም መረጃን በማቀበል ይሰራሉ ብሎ የጠረጠራቸውን በመንግስት መስሪቤቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎችንና አገዛዙን የሚነፍቁ የመገናኛ ብዙሀኖችንም እንደሚያካትት ታውቅዋል።

የወያኔ አገዛዝ እነኚህን አካላት በትሮጃን ሆርስ ቫይረስ ነው የመሰላቸው፣ የወያኔን አገዛዝ ስራ በማጋለጥ ውድቀቱን የሚያፋጥኑ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ወያኔ በፍትህ ሚኒስተር መስሪያ ቤት አንድ ግብረ አበር ቡድን ያቋቋመ ሲሆን አላማውም በፍትህ መኒስቴር መስሪያቤት ውስጥ በፖለቲካ እስረኞች ላይ የሚደርሰውን ኢሰብአዊ ድርጊትና ስልጣንን በመጠቀም የሚፈፀመውን ወንጀል በተመለከተ ለዜና አውታሮች መረጃዎችን የሚያቀብሉ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ለማዋል ነው።

የውስጥ ምንጮች እንደገለፁት ይሄው ቡድን በዋነኛነት በኦሮሞ የህግ ኤክስፐርቶች ላይ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ወደአሜሪካ ተሰደው የሚገኙት ከዚህ ቀደም የፍትህ ሚኒስተር ዳየሬክተር የነበሩትን የአቶ ለገሰ አለሙ ጉዋደኞች ላይ ያነጣጠረ ነው፣ ይህ ቡድን እነገርህን ግለሰቦች መረጃውን ለዜና አውታሮች ወይም ደግሞ ለአቶ ለገሰ ስለማቀበላቸው በምርመራ መልክ መጠየቃቸውም ታውቅዋል።

ከዚህም ባለፈ "አቶ ለገሰ በኢትዮጵያ መንግስት በጥብቅ የሚፈለግ ግለሰብ ነው፣ ግለሰቡ እጃችን ሲገባ በዚህ ተግባር ከተሳተፋችሁ ለክህደታችሁ ከፍላችሁ የማትጨረሱት እዳ ነው የሚከተላችሁ" የሚል ማስፈራሪያ ከባለስልጣናቱ እንደደረሰባቸውም ገልፀዋል።

ወያኔ ይህን ግብረአበር ቡድን ለማቋቋም የተገደደው ከፍትህ ሚኒሲተር በተደጋጋሚ ወጥተው በተለያዩ የዜና አውታሮች በታተሙት ሚስጢራዊ ዜናዎች ሲሆን ይህም በኦሮሞዎችና ሌሎችም ግለሰቦች ላይ የሀሰት ክስ በመመስረትና ለእስር በመዳረግ እንዲሁም ቶርች በማድረግ ትልቅ ሚና ሲጫወቱ የነበሩ የወያኔ አባለትን ያጋለጠ በመሆኑ ነው።

## የቤዱዊን ነጎዎች የኢትዮጵያ፣ የኤርትራና የሱዳን ስደተኞችን የውስጥ አካል እያወጡ እንደሚሸጡ ታወቀ

ሲኤን ኤን እንደዘገበው የሳይናይ በረሀን በማቋረጥ ወደ እስራኤል ለመጓዝ ሙከራ የሚያደርጉ ኢትዮጵያውያን፣ ሱዳንያውያንና ኤርትራዊያን አስፈላጊውን ክፍያ መፈጸም ካልቻሉ፣ የሆድ እቃቸው ተከፍቶ ኩላሊታቸው ና ጉበታቸው ከወጣ በሁዋላ፣ በዚያው እንዲሞቱ እንደሚደረጉ ዘግቧል።

ዘ ኒው ጀኔሬሺን ፋውንዴሽን ፎር ሁማን ራይትስ እናዘ ኤቭሪዋን ግሩፕ የተሰኙትን ድርጅቶች በመጥቀስ ሲኤን ኤን እንደዘገበው፣ ስደተኞቹ የተጠየቁትን በብዙ ሺ የሚቆጠር ክፍያ ለመፈጸም ካልቻሉ ወደ ሳይናይ በረሀ ይወሰዱና በህይወት እያሉ የሆድ እቃቸው በግብጽ ዶክተሮች ይከፈታል።

ስደተኞቹ ጉበታቸውና ኩላሊታቸው ከወጣ በሁዋላ ወዲያዉኑ እንደሚሞቱ፣ የስደተኞቹን አስከሬን በመመርመር ማረጋገጣቸውን ድርጅቶቹ ማረጋገጣቸውን የሲኤን ኤን ዘገባ ያመለክታል።

በቅርቡ በሳይናይ በረሀ የታሰሩ ከ70 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የድረሱልን ጥሪ ማሰማታቸውን መዘገባችን ይታወሳል። ባልታወቀ ስፍራ ታስረው ከሚገኙት ስደተኞች መካከል በርካታ ሴቶችና ወንዶች መደፈራቸውን፣ አንዳንዶች ህጻን ልጆችን የያዙ መሆናቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

አንድ ስደተኛ የሳይናይ በረሀን በማቋረጥ ወደ እስራኤል ለመግባት እስከ 20 ሺ ዶላር የሚደርስ ገንዘብ እንደሚጠዬቅ ስደተኞቹ ገልጠዋል።

## የቀድሞው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ፕሬዚዳንት የነበረው ያረጋል አይሸሹም . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የመለስ ዜናዊ ቡድን በስፋት እያራመደ ላለው የአገር ሃብት ዘረፋ ተባባሪ ለማብዛት ሂሊናቸው ከግላቸውና ከቤተሰቦቻቸው የማቴሪያል ጥቅም በላይ አርቆ ማየት የማይችል አቅመ ደካማ ሰዎችን በዙሪያው በማሰባሰብ እንደሚገለገልባቸው ሲዘገብ ቆይቶአል።

ወያኔ በበላይነት በሚያስተዳድረው የኢህአደግ አባል ድርጅቶች ውስጥ አባል በመሆናቸው የየክልላቸውን ሃብት ዘርፈው እንዲያዘርፉ ሥልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦች፤ በዘረፋ የሚበቃቸውን ሃብት ካከማቹ ቦኋላ በሎሌነት ከሚያገለግሉዋቸው የህወሃት ባለሥልጣናት ጋር ሲጋጩ እንደሚፈረደባቸው የጥፋት አይነት በውስጥ ግምገማ የዘረፉትን ሃብት ይዞ ይባረራሉ፤ ጥቂቶች ደግሞ እንደ ያረጋል አይሸሹም ጉዳያቸው ወደ ፍርድ ቤት ተመርቶ ኦሥር ቤት ይወረወራሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን ህወሃት ለሁለት በተከፈለበት ወቅት ለፖለቲካ ብቀላ በነ አቶ ስዬ አብረሃ ላይ ከተመሰረተው ውንጀላ በቀር እስከዛሬ አንድም ሰው ከህወሃት በግምገማ መባረሩ አደባባይ ስላላወጣ ሁሌ በግምገማ በሚታመሱ የኦህዴድና የብአዴን አባላት መካከል ከፍተኛ ቅሬታ ማስከተሉን ምንጮቻችን ይናገራሉ።

የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዘብ መስፈን በአገሪቱ ካሉት ባለሥልጣናት ሁሉ ከፍተኛ ድርሻ ባለው ሙስና ብዙ ሃብት ያፈራች መሆኗ ሲታወቅ ከአገር አልፎ በቅርቡ አንድ የስፔን ጋዜጣ ከአፍሪካ የመሪዎች ሚስት ተወዳዳሪ የሌላት ከበርቴ እንደሆነች መዘገቡ አይዘነጋም።

## ወያኔ ለከፋፍለህ ግዛ አላማው የሙስሊሙን ማህበረሰብ ለሁለት መከፈሉና . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ብሎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የነፍጠኛው መሸሸጊያ ሆናለች በማለት በውስጥ ችግር እንድትታመስና እንድትዳከም ማድረጉ በስፋት ሲዘገብ የቆየ ሲሆን አሁን ደግሞ ይሄው አባዜው አልለቀው ብሎት ፊቱን ወደ እስልምና ማዞሩ ታውቁአል።

የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰሞኑን በሙስሊሙ ህብረተሰብ መካከል እያካሄደ ያለውን ክፍፍል አስመልክቶ አስተያየታቸውን ለኢሳት የሰጡ የእምነቱ ተከታዮች፤ በምርጫ 97 ወቅት ኢህአዴግ የሙስሊሙ ጠበቃ እኔ ነኝ በማለት ቅስቀሳ ማድረጉን አውስተው፣ አሁን ደግሞ የሀይማኖቱን ተከታዮች ለሁለት ክፍሎ እርስ በርስ እንዲጋጩ ለማድረግ ጥረት እያደረገ መሆኑ አገዛዙ በምን አይነት ሃላፊነት የጎደለው አጥፊነት ሥራ እንደተሰማራ ያስገነዝባል ማለታቸውን ተዘግቦአል።

እነኚሁ አስተያየት ሰጪዎች በማጠቃለያቸው በኢትዮጵያ በሀይማኖቶች መካከል ለዘመናት የነበረው መቻቻል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ በመሄዱ ወያኔ አገሪቱን ሊፈነዳ በተቃረበ የእስተገሞራ አለት ላይ እንድትቀመጥ አድርጓታል ሲሉ ስጋታቸውን መግለጻቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

ወያኔ በሰሜን አፍሪካይቷ አገር በቱኒዚያ የፈነዳውና ወደ በርካታ የሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምስራቅ ሃገራት በተዛመተው ጸረ አምባገነኖች ህዝባዊ አብዮት እጅግ ስለተደናገጠ፤ በአገራችን ከመቀስቀሱ በፊት ህዝብ በጋራ እንዳይነሳበት የሚችለውን ዜዴ ሁሉ እየተጠቀመ እንደሆነ የሚናገሩት ከዚህም አንዱ በሃይማኖቶች መካከል ጣልቃ እየገባ አማኞችን እርስ በርስ ማጋጨት እንደሆነ ይስማማሉ።

## ጥቅምት 22 ቀን 1998 በአረመኔው የወያኔ አገዛዝ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ንቅናቄያችን ግንቦት ሰባት "የማንረሳው ወንጀልና የማንረሳቸው ሰማእታት" በሚል ረዕስ መግለጫ አውጥቱአል። ግንቦት 7 ባወጣው በዚህ መግለጫ " የዘንድሮውን 6ኛ አመት የጥቅምት 22 ሰማዕታት ቀን የሚንዘክረው፤ ሰማዕታቱ ህይወታቸውን የተሰውለትን መልካም አስተዳደር በአገራችን ለማስፈን ይቻል ዘንድ ለፍትህ፤፤ ለእኩልነትና ለነጻነት የሚደረገውን ትግል ከዳር ለማድረስ ያለንን ቁርጠኝነት እንደገና በማደስ፤ የኢጋዚን ጦር አሰልጥኖና አስታጥቆ በወገኖቻችን ላይ ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዲፈጸም መመሪያ የሰጡውን መለስ ዜናዊንና ጥቂት ግብረአበሮቹን በተባበረ ትግል ህግ ፊት ለማቅረብ ትግሉ የሚጠይቀውን ማንኛውንም መሰዋ ዕትነት ለመክፈል ቁርጠኝነታችንን ዝግጁነታችንን በመግለጽ ነው" ብሉአል።

## ህዝብን ማሸበር የመጨረሻዉን ቀን ያሳጥረዋል እንጂ አያስረዝመዉም . . . (ከገፅ 3 የዞረ)

ወረራ ዘመን ለጠላት አንገዛም ብለዉ መሳሪያ አንስተዉ ጠላትን ያንቀጠቀጡ ልጆቹን "ናደዉ" "ድል ነሳ" ና "አሸናፊ" ብሎ እንደሰየማቸዉ ዛሬም የወያኔን ዘረኝነት የሚታገሉ ልጆቹን ሽብሬ፤ ሽብሩ ወይም አሸብር እያለ እንደሚሰይማቸዉ ምንም ጥርጥር የለንም። ባለፉት አስር ወራት በግልፅ እንደተመለከትነዉ መለስ ዜናዊ ከቤን አሊ፤ ከሙባረክና በቅርቡ ደግሞ ጋዳፊን ከገጠማቸው የህዝብ ቁጣ ትምህርት መቅሰም የቻለ አይመስለንም፤ ተራው ደርሶ ላለፉት 20 አመታት ኮትኩቶ ያሳደጋቸው የህዝብ ብሶቶች ገንፍሎ አደባባይ ሲወጣ የሁላችንም ምኞትና ጸሎት የሚሆነው መለስ ዜናዊን አያድርገን ነው። እስከዚያው በወያኔ ፓርላማ ውስጥ ጭምር እያየነው ያለነው የመለስ ዜናዊ ድንፋታ፤ ስድቡና ፉከራ ይቀጥላል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz

እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:00 እስከ 2:30 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንዲታስታውቁን እንገልጻለን። ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org